# የፕሮግራም በጀት፣ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር /Annual Working Plan/ አቀራረብ መመሪያ /Guideline/

## /በፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና በልማት ድርጅቶች የሚተገበር/

የፕሮግራምና ፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት
ገንዘብ ሚኒስቴር
ሰኔ 2012

# ማውጫ

1. መግቢያ ..... 1

2. የመመሪያው /Guideline/ አስፈላጊነት ..... 2

3. የመመሪያው ወሰን ..... 3

4. የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድና አፈጻጸም አቀራረብ ..... 3

4.1. የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በተመለከተ ..... 3

4.1.1. ፕሮግራም በጀትን በተመለከተ ..... 4

i. የ2010-2012 የሶስት ዓመት አፈጻጸም ለማቅረብ፤ ..... 5

ii. የ….. በጀት ዓመት ዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት አፈጻጸም ለማቅረብ፣ ..... 9

iii. የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር በተመለከተ፣ ..... 11

4.1.2. ከልማት አጋሮች /Development Partners/ በተገኘ ገንዘብ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት አፈጻጸምና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር /Annual Working Plan/ ለማቅረብ ..... 15

4.1.3. የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ይዘት ..... 19

4.2. በልማት ድርጅቶች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ ..... 24

Annex: - Progress Report Templates for Programs and Projects Financed by Development Partners ..... 29

## 1. መግቢያ

የፌዴራል መንግስት የልማት ዕቅዱን ለማስፈጸም በበጀት፣ በውጭ ሀብት /ዕርዳታና ብድር/፣ በመልሶ ማበደር እና ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮች ከፍተኛ ሀብት በመመደብ በፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በክልሎች በኩል ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን እያስፈጸመ ይገኛል፡፡ ባለፉት ዓመታት በየደረጃው የሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመከታታል እንዲቻል የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚ አካላት እየተዘጋጁ ለሚኒስቴር መ/ቤታችን ለተለያዩ የስራ ክፍሎች እየቀረቡ በተበታተነ ሁኔታ ክትትልና ግምገማ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ **ዕቅድን ከበጀት፣ በጀትን ከወጪ፣ ወጪን ከውጤት፣ ውጤትን በበላይ አመራሩ ከሚደረግ ግምገማ ጋር ማስተሳሰርና ተጠያቂነት ማስፈን እንዲሁም ልምዶችን መቀመርና መማማር** ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በዚህም የባለፉት ዓመታት የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ግምገማ እንደሚያሳየው በአብዛኛው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ወጪ እና ጊዜ እንደማይጠናቀቁ ነው፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ከላይ የተገለጸውን ችግር በመቅረፍ በቀጣይ የፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ማሻሻል እንዲቻል **የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ስርዓት አዋጅ** በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ደግሞ **ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን የሚከታተልና የሚገመግም ራሱን የቻል የስራ ክፍል እንዲቋቋም** ሆኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቀጣይ አዋጁን መሰረት በማድረግ የተጠቃለለ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ለመንግስት የሚቀርብ በመሆኑ በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች በበላይ አመራሩ ትኩረት አግኝተው የሚፈቱ ይሆናል፡፡

ስለሆነም በፌዴራል ደረጃ እየተተገበሩ የሚገኙ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ስርዓት አዋጅ መሰረት ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ጠንካራ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በማሻሻል በተያዘላቸው ጊዜና ወጪ በማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸውን ውጤት ማሳካት እንዲቻል በዚህ መመሪያ መሰረት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድ /Annual Working Plan/ እስከ ሐምሌ 30/2012፣
- የ2013 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ወስጥ፤

ለገንዘብ ሚኒስቴር የፕሮግራምና ፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

የአፈጻጸምና ዕቅድ ሪፖርቱን የሚያቀርበው መ/ቤት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤት ከሆነ የሚቀርበው ሪፖርት **በፕሮግራም በጀት እና በልማት አጋሮች /Development Partners/ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ያካተተ መሆን** የሚገባው ሲሆን ከገጽ 17-21 በቀረበው የሪፖርት አቀራረብ ይዘት መሰረት ሊቀርብ ይገባል፡፡ የአፈጻጸምና ዕቅድ ሪፖርቱን የሚያቀርበው የፌዴራል የልማት ድርጅት ከሆነ በልማት ድርጅቱ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ለእያንዳንዳቸው ከገጽ 22-26 መሰረት የፕሮጀክቶቹ አፈጻጸምና ዕቅድ ሊቀርብ ይገባል፡፡

***በተጨማሪም የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም በሚቀርብበት ወቅት ፕሮግራሙ ወይም ፕሮጀክቱ በልማት አጋር የሚደገፍ ከሆነ የስምምነት ሰነድ፤ፕሮጀክቱ የግንባታ ፕሮጀክት ከሆነ የኮንትራት ስምምነት ሰነዱ ስካን /scan/ ተደርጎ በሶፍት ኮፒ መቅረብ ይገባዋል፡፡***

## 2. የመመሪያው /Guideline/ አስፈላጊነት

የመንግስት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ከተተገበሩ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ በመሆን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠን ወሳኝ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ በሀገራችን በተለይ በቅርብ ዓመታት በፌዴራል መንግስቱ በኩል ከፍተኛ ሀብት በመመደብ በርካታ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በባለበጀት መ/ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በክልሎች በኩል እየተተገበሩ ይገኛል፡፡ ሆኖም በሀገራችን እየተተገበሩ በሚገኙ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ በተለያዩ ተቋማት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት በአብዛኛው በተያዘላቸው ወጪና ጊዜ እንደማይጠናቀቁና የሚጠበቅባቸውን

ውጤት በሚፈለገው ደረጃ እያሳኩ እንዳልሆነ ያሳያሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት አለመኖር እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

ስለሆነም ከላይ የተገለጸውን ችግር በመፍታት የፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ማሻሻል እንዲቻል ከዚህ በፊት በተበታተነ እና በተወሰኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ሲደረግ የነበረውን የክትትልና ግምገማ ስራ ወጥነት ባለው መልኩ በሁሉም ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ እንዲተገበር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ከዚህ በፊት ለሚኒስቴር መ/ቤታችን ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ለየፕሮግራሞቹና ለየፕሮጀክቶቹ **በተናጠል ሲቀርብ** የነበረውን የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና የስራ መርሃ ግብር ሪፖርቶች **በማስቀረት** ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ባለበጀት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በስራቸው ለሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የዓመታዊና የየሩብ ዓመት አፈጻጸምና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርቶች **በአንድ በተጠቃለለ ሰነድ** ማቅረብ ያለባቸው በመሆኑ ይህንን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 3. የመመሪያው ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል መንግስት በጀት፣ በውጭ ሀብት /ዕርዳታና ብድር/፣ በመልሶ ማበደር በመንግስት ዋስትና እና ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮች ወጪያቸው የሚሸፈኑ በባለበጀት መ/ቤቶችና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ይመለከታል፡፡

## 4. የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድና አፈጻጸም አቀራረብ

### 4.1. የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶችን በተመለከተ፣

ባለፉት ዓመታት እና በ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በፕሮግራም በጀት አሰራር ስርዓት መሰረት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር፣ የዓመታዊና የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በገንዘብ ሚኒስቴር ለበጀት ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በልማት አጋሮች ወጪያቸው ለሚሸፈኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ደግሞ በተናጠል ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ሲቀርብ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ሆኖም ይህ አሰራር በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ፋይናንስ የሚደረጉ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለው መልኩ

ለመገምገም ያስቸገረ በመሆኑ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በሚገባቸው መጠን መከታተልና መገምገማ ሳይቻል ቆይቷል፡፡

ስለሆነም ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ለሚኒስቴር መ/ቤታችን የሚቀርቡ የዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርቶች በተናጠል ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ሲቀርብ የነበረውን በማስቀረት በቀጣይ የፕሮግራም በጀት ሆነ በልማት አጋሮች በዕርዳታና በብድር ለሚሸፈኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም፣ የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ እና የ2013 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርቶች ለሚኒስቴር መ/ቤታችን ሲቀርብ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን በማካተት በአንድ ሰነድ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል፡፡

### 4.1.1. ፕሮግራም በጀትን በተመለከተ

ከባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ እየተተገበረ የሚገኘው የፕሮግራም በጀት ስርዓት ዋና ዓላማ የፕሮግራም አደረጃጀት /Program Based/ እና የውጤታማነት መረጃን /Key Performance Information/ በመጠቀም ውስን የሆነውን ሀብት ለውጤት በመመደብ፣ በመከታተልና በመገምገም የተመደበው ሀብት ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት በፕሮግራም በጀት ስርዓት የተመደበውን ሀብት ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈጻሚ መ/ቤቶች በየሶስት ዓመቱ፣ በየዓመቱና በየሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርቶች እንዲያቀርቡ እየተደረገ በተወሰነ ደረጃ ቢሆን ክትትልና ግምገማ ሲደረግ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለበጀት ዓመቱ በተመደበ በጀት የሚሰሩ ስራዎች ላይ ክትትል ማድረግ እንዲቻል በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አስፈጻሚ መ/ቤቶች ራሱን የቻለ ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት እስከ ሐምሌ 30 ድረስ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ሲደረግ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ የሪፖርት አቀራረብ ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ በተወሰነ ደረጃ እንደሚከተለው ተቀይሯል፡፡

- ባለፉት ዓመት በተለይ የፕሮግራም በጀት ስርዓት ከተጀመረ ጀምሮ ባለበጀት መ/ቤቶች አዲስ በጀት ዓመት ሲጀመር የአዲሱን በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት እስከ ሐምሌ 30/ እና የተጠናቀቀውን በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት እስከ ነሐሴ 15/ ድረስ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ አሰራር በባለበጀት መ/ቤቶች በተለይም በዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም የስራ ክፍሎች ላይ ጫና ያሳደረ በመሆኑ እና የሚቀርቡት ሪፖርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ

እንዳይሆኑ የራሱን አስተዋጽዖ እያደረገ በመሆኑ እንዲሁም ለአሳስፈላጊ የሀብት ብክነት እየዳረገ የሚገኝ በመሆኑ ***በቀጣይ የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር እና የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርቶች ሲቀርቡ በተናጠል ተዘጋጅተው ይቀርቡ የነበረውን በማስቀረት በአንድ ሰነድ የሚቀርቡ ይሆናል፡፡*** ስለሆነም ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ከዚህ በፊት በተናጠል ሲቀርቡ የነበሩ ዓመታዊ የአፈጻጸም እና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርቶች በአንድ ሰነድ /የ2012 ዓመታዊ አፈጻጸምና የ2013 ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት በሚል/ ተዘጋጅቶ እስከ ሐምሌ 30/2012 ድረስ ለመ/ቤታችን የሚቀርብ ይሆናል፡፡

- የ2012 በጀት ዓመት የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት ሳይክል አካል ሲሆን ይህ ሳይክል ሰኔ 30/2012 ላይ የሚያበቃ ይሆናል፡፡ ይህም በ2010 በጀት ዓመት በስራ ላይ የነበሩ ነባር መ/ቤቶች የ2012 ዓመታዊ አፈጻጸምና የ2013 ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት ሲያቀርቡ በ2009 በጀት ዓመት በዓላማ /Outcome/ ደረጃ ለየፕሮግራሞቹ ለሶስት ዓመት /ለ2010-2012/ የታቀደውን በመገምገም የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት አፈጻጸም ተካቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት፣ የዓመታዊ፣ የግማሽ ዓመት እና የሩብ ዓመት አፈጻጸምን እና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብርን ለማቅረብ የሚከተለውን የማቅረቢያ ፎርማቶች ወይም ቅጾች መጠቀም ግድ ይላል፡፡

**i. የ2010-2012 የሶስት ዓመት አፈጻጸም ለማቅረብ፤**

የ2010-2012 *ዕቅድ የታቀደላቸው ነባር መ/ቤቶች ሰንጠረዥ* 1፣ ሰንጠረዥ 2 እና ሰንጠረዥ 3 በመጠቀም የሶስት ዓመት አፈጻጸም ማቅረብ ይጠብቅባቸዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡ የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት የፕሮግራሞች አፈጻጸም ማጠቃለያ ማቅረቢያ**

| የፕሮግራም ስም/ የፕሮግራም ዓላማ ዕቅድ | የፕሮግራሙ ዓላማ የ2010-2012 የፊዚካል ስራ አፈጻጸም | የ2010-2012 የፋይናንስ አፈጻጸም በሚሊዮን ብር | | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | አፈጻጸም | |
| **ፕሮግራም 2፡ ስም**<br>ለ2010-2012 | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የታቀደውን ዓላማ እዚህ ይገለጽ | | | | |
| ፕሮግራም 3፡ ስም ዓላማው እዚህ ይገለጽ | | | | |
| ፕሮግራም 4፡ ዓላማው እዚህ ይገለጽ | | | | |

## ሰንጠረዥ 2፡- የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ

በሚሊዮን ብር

| የፕሮግራም ስም/ የፕሮግራም ውጤት መግለጫ | ለ2010-2012 የታቀደ | | | የ2010-2012 አፈጻጸም | | | | የ2010 ክንውን | | የ2011 ክንውን | | የ2012 ክንውን | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መለኪያ | ግብ | ወጪ | ግብ | የግብ አፈጻጸም በመቶኛ | ወጪ | የወጪ አፈጻጸም በመቶኛ | ግብ | ወጪ | ግብ | ወጪ | ግብ | ወጪ |
| ፕሮግራም 1፡ ስም<br>ለ2010-2012 የታቀደ ውጤቶች | | | | | | | | | | | | | |
| ፕሮግራም 2፡ ስም<br>ለ2010-2012 የታቀደ ውጤቶች | | | | | | | | | | | | | |
| ፕሮግራም 3፡<br>ለ2010-2012 የታቀደ ውጤቶች | | | | | | | | | | | | | |

## ሰንጠረዥ 3፡- በ2010፣ በ2011 እና በ2012 በጀት ዓመት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ[1]

| የፕሮጀክቶች ስም | ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ በሚሊዮን ብር | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከስራ ተቋራጩ ጋር በመጀመሪያ ስምምነት የተደረገበት ዋጋ | ለስራ ተቋራጩ የተከፈለ | ለካሳ ክፍያ የተከፈለ | |
| በ2010 የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች<br>1.<br>2.<br>3.<br>ወዘተ | | | | | |
| በ2011 የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች<br>1.<br>2.<br>3.<br>ወዘተ | | | | | |
| በ2012 የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች<br>1.<br>2.<br>3.<br>ወዘተ | | | | | |

[1] የግንባታ ፕሮጀክቶችን ብቻ የሚመለከት

**ii. የ..... በጀት ዓመት ዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት አፈጻጸም ለማቅረብ፣**

የ........በጀት ዓመት ዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ለማቅረብ ሰንጠረዥ 4 እና ሰንጠረዥ 5 በመጠቀም መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- የ....... በጀት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ**

| **የፕሮግራም/የውጤት ስም** | **የውጤት መለኪያ** | **የ...... በጀት ዓመት የፊዚካል** | | **የ...... በጀት ዓመት ፋይናንስ /በሚሊዮን ብር/** | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | **ዕቅድ** | **አፈጻጸም** | **ዕቅድ** | **አፈጻጸም** |
| ፕሮግራም 1 | | | | | |
| ፕሮግራም 2<br>ውጤት 1 ስም፡-<br>ውጤት 2 ስም፡- | | | | | |
| ፕሮግራም 3 ስም<br>ውጤት 1 ስም፡-<br>ወዘተ | | | | | |

ሰንጠረዥ 5፡- የ........ በጀት ዓመት ዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ[2]

/በሚሊዮን ብር/

| *የፕሮጀክቱ መለያ ኮድ /በበጀት አዋጁ መሰረት/* | *የፕሮግራሙ/የፕሮጀክቱ /የኮምፖኔንቱ/ ስም* | *የሚሰራበት ቦታ* | *የተጀመረበት ወርና ዓመት* | የሚጠናቀቅበት ወርና ዓመት | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ የፊዚካል ዕቅድ | ለካሳ ክፍያ የተከፈለ | እስከ ...... መጨረሻ ድረስ የወጣ ወጪ /ካሳ ክፍያን ሳይጨምር/ /Expenditure To Date/ | እስከ ....... መጨረሻ የተሰራ የፊዚካል ሥራዎች የአፈጻጸም ደረጃ | *በ...... የተሰራ የፊዚካል ዕቅድ አፈጻጸም* | *ለ....... በጀት ዓመት ወጪ የተደረገ* |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጀመሪያው ዕቅድ /Original Plan/ | *ዕቅዱ ከተሻሻለ* /Revised Plan/ | በመጀመሪያው ዕቅድ /Original Plan/ | *ዕቅዱ ከተሻሻለ* /Revised Plan/ | | | | | | |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | | | | | | | | | | | |
| | ***የፕሮግራም 1 ስም*** | | | | | | | | | | | | |
| | **የፕሮጀክት 1 ስም** | | | | | | | | | | | | |
| | **ወዘተ** | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

[2] ፕሮጀክቱ በጥቅል የተፈቀደ ፕሮጀክት ከሆነ በስሩ ላሉ ኮምፖኔንቶች የፕሮጀክት መግለጫ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል።

### iii. የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር በተመለከተ፣

ባለፉት ዓመታት በፕሮግራም በጀት ስርዓት መሰረት ባለበጀት መ/ቤቶች አዲስ የበጀት ዓመት በሚጀምርበት ወቅት ራሱን የቻለ ዓመታዊ የስራ ምርሃ ግብር ሪፖርት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ሲደረግ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ሆኖም ይህ አካሄድ *በባለበጀት መ/ቤቶች ላይ አላስፈላጊ ጫና እያስከተለ በመሆኑ ከ2013 ጀምሮ ብቻውን መቅረቡ ቀርቶ የአፈጻጸም ሪፖርቱ አካል ሆነ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም በሚቀርብበት ወቅት የሚከተሉትን ሰንጠረዦች /ሰንጠረዥ 6፣ 7 እና 8/ በማካተት የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርህ ግብር ማቅረብ ይገባል፡፡*

ባለበጀት መ/ቤቶች ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር እንዲያቀርቡ የሚደረገው ለአዲሱ በጀት ዓመት በተመደበው በጀት ሊተገበሩ የታቀዱ ስራዎችን ለመከታተል እንዲያመች ነው፡፡ በመሆኑም የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት ሲቀርብ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት መጠናቀቅ የነበረባቸው ነገር ግን ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች እንዲሁም በተያዘላቸው እቅድ መሰረት እየተከናወኑ ያለሆኑ ፕሮጀክቶች ተለይተው በሰንጠረዥ 8 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መቅረብ ይገባዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- የ2013 በጀት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ማቅረቢያ**

| የፕሮግራም/የውጤት ስም | የውጤት መለኪያ | የ2013 በጀት ዓመት የፊዚካል ዕቅድ | | | | የ2013 በጀት ዓመት ፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር/ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ና ሩብ ዓመት |
| ፕሮግራም 1 | | | | | | | | | |
| ፕሮግራም 2<br>ውጤት 1 ስም፡-<br>ውጤት 2 ስም፡- | | | | | | | | | |
| ፕሮግራም 3 ስም<br>ውጤት 1 | | | | | | | | | |

| ስም፡-<br>ወዘተ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

## ሰንጠረዥ 7፡- የ2013 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ማቅረቢያ /በሚሊዮን ብር/[3]

| የበጀት ኮድ | የፕሮጀክት ስም | የሚሰራት ቦታ | የተጀመረበት ወርና ዓ.ም | የሚጠናቀቅበት ወርና ዓ.ም | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዕቅድ | | የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ | | | | የፋይናንስ ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጀመሪያው ዕቅድ /Original Plan/ | በተስተካከለው ዕቅድ (ዕቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/ | በመጀመሪያ ዕቅድ /Original Plan/ | በተሻሻለው ዕቅድ (ዕቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/ | መለኪያ | የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |

[3] ፕሮጀክቱ በስሩ ኮምፖኔንት ካለው ለእያንዳንዱ ኮምፖኔንት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡- የ2013 በጀት ዓመት ሩብ /ግማሽ/ ዓማታዊ/ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ማቅረቢያ**

| የበጀት ኮድ | የፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ስም | ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ | ትኩረት/ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች | ችግሩ እንዲፈታ የሚጠበቅበት ጊዜ | ችግሩን ለመፍታት በአስፈፃሚው መ/ቤት የተወሰደ እርምጃ | ችግሩን ለመፍታት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

**ማሳሰቢያ፡-** በዚህ ሰንጠረዥ የሚጠናቀቁበት ጊዜ ያለፋቸው፣ የዘገዩ እና በቀጣይ ችግር ሊገጥማቸው የሚችሉ ፕሮጀክቶች በአግባቡ ግምገማ ተካሂዶ መረጃው ሊቀርብ ይገባል፡፡

### 4.1.2. ከልማት አጋሮች /Development Partners/ በተገኘ ገንዘብ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የዓመታዊ /ግማሽ/ ሩብ/ ዓመት አፈጻጸምና ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር /Annual Working Plan/ ለማቅረብ

ከልማት አጋሮች በሚገኝ ሀብት ወጪያቸው የሚሸፈኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አብዛኛዎቹ በፕሮግራም በጀት ስርዓት ውስጥ ተካተው በበጀት የሚጸድቁ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም በልማት አጋሮች የሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተለያዩ የወጪ አሸፋፈን አማራጮችን የሚጠቀሙ መሆናቸው /ቻናል አንድ፣ ቻናል ሁለት/ እና ፕሮግራሞቹንና ፕሮጀክቶቹን በፋይናንስ የሚደግፉ አካላት የተለየ የአፈጻጸም ሪፖርት የሚጠይቁ በመሆናቸው እንዲሁም ለፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማቅረቢያ በተቀረጹ ፎርማቶች /ቅጾች/ አፈጻጸማቸውን ለማቅረብ የሚያስቸግር በመሆኑ በልማት አጋሮች የሚደገፉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በልዩ ሁኔታ ሰንጠረዥ 9 እና ሰንጠረዥ 10 በመጠቀም መቅረብ ይገባዋል፡፡ ሰንጠረዥ 10 ለእያንዳንዱ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት የሚዘጋጅ ነው፡፡

ስለሆነም የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም በሚቀርብበት ወቅት በልማት አጋሮች ድጋፍ እየተተገበሩ ያሉ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ሁሉንም በሰንጠረዥ 9 በዝርዝር ማቅረብ የሚገባ ሲሆን የእያንዳንዱን ፕሮግራምና ፕሮጀክት አፈጻጸም ደግሞ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ሰንጠረዥ 10 አፈጻጸሙን ማቅረብ ይገባል፡፡ ***/በስምምነቱ መሰረት አስፈጻሚው አካል የፕሮጀክቱን ወይም የፕሮግራሙን ወጪ ለሚሸፍነው የልማት አጋር ሪፖርት የሚያቀርብ ከሆነ ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚላከው ሪፖርት በእንግሊዘኛ መሆን አለበት፡፡ የእንግሊዘኛው የማቅረቢያ ፎርማት በአባሪ መልክ ተያይዟል፡፡/***

## ሰንጠረዥ 9፡- የ…….በጀት ዓመት ዓመታዊ/ግማሽ/ሩብ ዓመት በልማት አጋሮች ድጋፍ እየተተገበሩ ያሉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማጠቃለያ /Summary/ ማቅረቢያ /in Millions/

| የፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ስም | ዕርዳታ/ብድር የሰጠው አካላ /Name of Doners/ | ስምምነት የተደረገበ ት የገንዘብ ዓይነት/ USD, Euro, Yen or …./ | ስምምነቱ የሚቆይበ ት ዘመን | ጠቅላላ በስምምነቱ የሚገኝ ገንዘብ መጠን /Total Aid or Loan/ | እስከ 2012 መጨረሻ ድረስ ለፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ የፈሰሰ /Expenditure to date/ | በ2012 በጀት ዓመት ብቻ ለፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ የፈሰሰ /Expenditure in 2012 budget year/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | |
| 2. | | | | | | |
| 3. | | | | | | |
| 4. ወዘተ | | | | | | |

## ሰንጠረዥ 10፡- የ……በጀት ዓመት በልማት አጋሮች የሚደገፉ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክት የዓመት /የሩብ/ የግማሽ/ አፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርብበት ቅጽ[4]

1. **የፕሮግራም/ ፕሮጀክት መግለጫ /Program and Project Profile/**

| | |
|---|---|
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት ስም | |
| የፕሮግራሙ/ፕሮጀክት ዘመን ፡ /በስምነቱ መሰረት/ | |
| ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ: | |
| ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ: | |
| ከፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ውጤቶች (የግብ ስኬቶች)፡ | |
| የገንዘብ ምንጭ | |
| ጠቅላላ በጀት /In millions USD, Euro | |

[4] ይህ ቅጽ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 8 ያሉትን ያካትታል።

| | |
|---|---|
| or other currency as per the agreement/ | |
| በመንግስት የሚሸፈን መጠን | |
| የሚተገበርበት ቦታ | |
| ፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ | |
| ባለድርሻ አካላት | |

2. **የፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ዝርዝር መግለጫ**

 2.1. መግቢያ፡

- ስለ ፕሮጀክቱ ምንነት አጭር ገለጻ
- በፕሮጀክቱ ምን ለማግኘት እንደታሰበ ጠቅለል ያለ ሐሳብ
- በሪፖርቱ ጊዜ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች

3. በፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ የተገኙ ዋና ዋና ስኬቶች

 3.1. ዓላማ 1

 3.2. ዓላማ 2

 3.3. ዓለማ 3

4. **የፊዚካል አፈጻጸም** ( ይህ ክፍል የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራትን፣ በመለኪያ/መስፈርያ የተብራራ አፈጻጸም፣ ወዘተ ያቀርባል)

| **የፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ በኮምፖንቶች፣ በዋና ዋና ተግባራት ወይም በውጤት** | **መለኪያ** | **የበጀት ዓመቱ ዕቅድ** | **የበጀት ዓመቱ ክንውን** | **የበጀት ዓመቱ ክንውን በ%** | **ፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ከተጀመረ እስከ አሁን ያለው ክንውን በ%** | **ተጨማሪ መግለጫ** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

5. የፋይናንስ አፈጻጸም

| የፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ በኮምፖንቶች፣ በዋና ዋና ተግባራት ወይም በውጤት | የገንዘቡ አይነት /Currency/ | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | የበጀት ዓመቱ ክንውን | የበጀት ዓመቱ ክንውን በ% | ፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ከተጀመረ እስከ አሁን ያለው ክንውን በ% | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

6. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

| ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ | ትኩረት/ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች | ችግሩ እንዲፈታ የሚጠበቅበት ጊዜ | ችግሩን ለመፍታት በአስፈፃሚው መ/ቤት የተወሰደ እርምጃ | ችግሩን ለመፍታት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት አካል |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

7. በሪፖርቱ ጊዜ የተገኙ ትምህርቶች

8. የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ዕቅድ /Annual Working Plan/[5]

| የፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ኮምፖንቶችና ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የፊዚካል ዕቅድ | | | | የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን usd/euro..etc/ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

## 4.1.3. የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ይዘት

ከላይ እንደተገለፀው የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድ፣ የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲዘጋጅና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርብ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በወጣው የፌዴራል መንግስት የፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ስርዓት አዋጅ ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በየሩብ ዓመትና በዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመረጃና በአንዳንድ ጉዳዮች ልዩነቶች ሊኖሩ ቢችሉም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ይዘት ግን ተመሳሳይ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ይህም በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ትኩረት በማድረግ ተቋማትን በተሟላ ሁኔታ ለመገምገም በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

በመሆኑም በተቋማት የሚዘጋጀውና የሚላከው የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የሚከተሉት ይዘቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

[5] በዓመት ለአንድ ጊዜ ተዘጋጅቶች የሚቀርብ ነው፡፡

### 4.1.3.1. የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት፣ የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸምና የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት ይዘት

ባለበጀት መ/ቤቶች የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም፣ የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት እስከ ሐምሌ 30/2012 ድረስ መቅረብ ያለበት ሲሆን የሚቀርበው ሪፖርት የሚከተለው ይዘት ሊኖረው ይገባል፡፡

1. **ድርሞ** /Executive Summary/

ይህ የሪፖርቱ ክፍል ዋናው ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ የሚፃፍ ነው፣

- ዋና ዋና አመልካቾችን መሠረት ያደረገ የዕቅድ አፈፃፀምን እንዲያሳይም ይጠበቃል፣ የተመደበው በጀት እና አፈፃፀሙ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በአጭሩ ማሳየት አለበት፣
- መደምደሚያዎች፣ ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችና ምክረ ሃሳቦችን ያካትታል፣
- በዚህ ክፍል ዝርዝር ትንተና አስፈላጊ አይደለም በመሆኑም ይህ ክፍል ከጠቅላላው የሪፖርቱ የገፅ ብዛት ከ10 በመቶ እንዳይበልጥ ይመከራል፡፡

2. **የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት /2010-2012/ አፈጻጸም**

በዚህ ክፍል ሰንጠረዥ 1፣ 2 እና 3 በአግባቡ መረጃዎችን በመሙላትና በዚህ ክፍል በማካተት የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት አፈጻጸም በዓላማ ደረጃ /Outcome Level/ አጭር ትንተና የሚቀርብበት ነው፡፡

- ሰንጠረዥ 1፡- የፕሮግራም በጀት የሶስት ዓመት የፕሮግራሞች የዓላማ አፈጻጸም ማጠቃለያ ማቅረቢያ
- ሰንጠረዥ 2፡- የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ
- ሰንጠረዥ 3፡- በ2010፣ በ2011 እና በ2012 በጀት ዓመት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ

3. **የ2012 ዓመታዊ አፈጻጸም**

በዚህ ክፍል የ2012 ዓመታዊ አፈጻጸም የፕሮግራም በጀትን በተመለከተ ሰንጠረዥ 4 እና 5 በአግባቡ በመሙላት በዋና ዋና ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ መሰረት በማድረግ አጭር

ትንተና የሚቀርብበት ነው። ባለበጀት መ/ቤቱ በልማት አጋሮች /Development Partners or Doners/ የሚደገፉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እያስፈጸም የሚገኝ ከሆነ ዓመታዊ አፈጻጸማቸው በዚህ ክፍል ሰንጠረዥ 9 እና 10 በመጠቀም መቅረብ ይኖርበታል። በዚህ መሰረት የሚከተሉት ሰንጠረዦች በአግባቡ መረጃዎች ተሞልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

- ሰንጠረዥ 4፡- የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ
- ሰንጠረዥ 5፡- በ2012 በጀት እየተተገበሩ የነበሩ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ
- ሰንጠረዥ 9፡- በ2012 በልማት አጋሮች ድጋፍ እየተተገበሩ የነበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማጠቃለያ ማቅረቢያ /in Millions/
- ሰንጠረዥ 10፡- በልማት አጋሮች የሚደገፉ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክት የዓመት /የሩብ/ የግማሽ/ አፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርብበት ቅጽ፣

4. **የ2013 በጀት ዓመት የስራ መርሃ ግብር** /Annual Working Plan/

በዚህ ክፍል በክፍል ሶስት የቀረበውን የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና ለ2013 በጀት ዓመት የጸደቀውን በጀት መሰረት በማድረግ በ2013 በጀት ዓመት የሚሰሩ ስራዎች በሩብ ዓመት ተከፋፍሎ የሚቀርብበት ነው። የሚከተሉት ሰንጠረዦች መጠቀም የግድ ይላል።

- ሰንጠረዥ 6፡- የ2013 በጀት ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ማቅረቢያ
- ሰንጠረዥ 7፡- የ2013 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር ማቅረቢያ /በሚሊዮን ብር/
- ሰንጠረዥ 8፡- የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ማቅረቢያ

5. **በ2012 ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱና ሊውሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች**
6. **ማጠቃለያ**
7. **አባሪ**
    - ፕሮግራሙ ወይም ፕሮጀክቱ በልማት አጋር የሚደገፍ ከሆነ የስምምነት ሰነድ፤
    - ፕሮጀክቱ የግንባታ ፕሮጀክት ከሆነ የኮንትራት ስምምነት ሰነዱ ስካን /scan/ ተደርጎ በሶፍት ኮፒ መቅረብ ይገባዋል።

### 4.1.3.2. የ2013 በጀት ዓመት የ……ሩብ /ግማሽ ዓመት/ አፈጻጸም ሪፖርት ይዘት

ባለበጀት መ/ቤቶች የ2013 በጀት ዓመት የየ…ሩብ ዓመት አፈጻጸም የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ውስጥ የሚከተለውን ይዘት በማሟላት መቅረብ ይገባዋል፡፡

1. **ድርሞ** /Executive Summary/

ይህ የሪፖርቱ ክፍል ዋናው ሪፖርት ከተዘጋጀ በኂላ የሚፃፍ ነው፣

- ዋና ዋና አመልካቾችን መሠረት ያደረገ የዕቅድ አፈፃፀምን እንዲያሳይም ይጠበቃል፣ የተመደበው በጀት እና አፈፃፀሙ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በአጭሩ ማሳየት አለበት፣
- መደምደሚያዎች፣ ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችና ምክረ ሃሳቦችን ያካትታል፣
- በዚህ ክፍል ዝርዝር ትንተና አስፈላጊ አይደለም በመሆኑም ይህ ክፍል ከጠቅላላው የሪፖርቱ የገፅ ብዛት ከ10 በመቶ እንዳይበልጥ ይመከራል፡፡

2. **የ2013 በጀት ዓመት የየ….ሩብ /ግማሽ ዓመት/ አፈጻጸም**

በዚህ ክፍል የ2013 የየ…ሩብ /ግማሽ/ ዓመት አፈጻጸም ሰንጠረዥ 3፣ 4፣ 7፣ 8 እና 9 በአግባቡ በመሙላት በዋና ዋና ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ መሰረት በማድረግ አጭር ትንተና የሚቀርብበት ነው፡፡ በልማት አጋሮች /Development Partners or Doners/ የሚደገፉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ለእያንዳንዳቸው በዚህ ክፍል ሰንጠረዥ 8 እና 9 በመጠቀም አፈጻጸማቸው መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የሚከተሉት ሰንጠረዦች በአግባቡ መረጃቸው ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

- ሰንጠረዥ 4፡- የ2013 በጀት ዓመት የ…..ሩብ /ግማሽ/ ዓመት የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም ማቅረቢያ፣
- ሰንጠረዥ 5፡- በ2013 በጀት ዓመት እየተተገበሩ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የ…..ሩብ /ግማሽ/ ዓመት አፈጻጸም ማቅረቢያ /በሚሊዮን ብር/
- ሰንጠረዥ 8፡- የ……..ሩብ /ግማሽ/ ዓመት የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ማቅረቢያ፣

- ሰንጠረዥ 9፡- በ……በጀት ዓመት በልማት አጋሮች ድጋፍ እየተተገበሩ የነበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማጠቃለያ ማቅረቢያ /in Millions/፣
- ሰንጠረዥ 10፡- በ…..በጀት ዓመት በልማት አጋሮች የሚደገፉ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክት የዓመት /የሩብ/ የግማሽ/ አፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርብበት ቅጽ፣

## 4.2. በልማት ድርጅቶች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ

ባለፉት ዓመታት የፌዴራል መንግስቱ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ከውጭ ሀገር የተበደረውን መልሶ በማበደር፣ ከሼባ ቦንድ /Sheba Bond/፣ ከተለያዩ ልዩ ልዩ ፈንዶች /Special Funds/፣ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ለሚገኝ ብድር ዋስትና /Guaranty/ በመስጠት የልማት ድርጅቶች ብድር እንዲያገኙ በማድረግና ከፍተኛ ሀብት በመመደብ በርካታ ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ እያደረገ ይገኛል። በልማት ድርጅቶች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በባለበጀት መ/ቤቶች በኩል እንደሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ማፋጠን የሚጠበቅባቸው ሲሆን በባለበጀት መ/ቤቶች ከሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በተለየ ደግሞ ፕሮጀክቶችን ለማከናወን የተወሰደን ብድር በአግባቡ መልሰው መክፈል ይጠበቅባቸዋል። ይህም በልማት ድርጅቶች በኩል የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በባለበጀት መ/ቤቶች ከሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በተለየ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊተገበሩ እና ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ግምገማ ሊካሄድባቸው የሚገባ መሆኑን ያሳያል።

ስለሆነም ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ የልማት ድርጅቶች በቅርቡ በጸደቀው የመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ስርዓት አዋጅ መሰረት ፕሮጀክቶቻቸው መምራት የሚገባቸው ሲሆን በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም መከታተልና መገምገም እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ለመንግስት ማቅረብ እንዲቻል **በስራቸው የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸምና የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የስራ መርሃ ግብር /Annual Working Plan/ እስከ ሐምሌ 30/2012 ድረስ እንዲሁም የ2013 በጀት ዓመት የሩብ/ግማሽ ዓመት አፈጻጸም ደግሞ ሩብ ዓመቱ ወይም ግማሽ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ውስጥ** የሚከተለውን ሰንጠረዥ ወይም ቅጽ /ከአንድ እስከ ስምንት ያሉትን ነጥቦች መሰረት በማደረግ/ ለእያንዳንድ ፕሮጀክት በማዘጋጀት ለገንዘብ ሚኒስቴር ወቅቱን ጠብቆ መቅረብ ይገባዋል። /የልማት ድርጅቱ ለምሳሌ አራት /4/ ፕሮጀክቶች ካሉት ለእያንዳንዳቸው ሰንጠረዥ ወይም ቅጽ እስራአንድን /11/ አራት ጊዜ በመጠቀም አፈጻጸማቸውን ማቅረብ ይገባል።/

## ሰንጠረዥ 11፡- በልማት ድርጅቶች የሚተገበሩ ፕሮጀክት የዓመት /የሩብ/ የግማሽ/ አፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርብበት ቅጽ[6]

### 1. ፕሮጀክት መግለጫ /Project Profile/

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክት ስም | | | |
| ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ: | | | |
| ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ /በመጀመሪያው ዕቅድ/ Original Plan/ | | | |
| ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ /ከተለከሰ/ Revised Plan | | | |
| የገንዘብ ምንጭ /የፕሮጀክቱ ወጪ የሚሸፈንበትን ይምረጡ/ | ከመልሶ ማበደር /ከሼባ ቦንድ/ ከልዩ ልዩ ፈንዶች/ | ከውጭ ሀገር ብድር በዋስትና | ከሀገር ውስጥ ብድር በዋስትና |
| ጠቅላላ ወጪ /በመጀመሪያው ዕቅድ Original Plan/ | /In millions USD, Euro or other currency as per the agreement or Birr/ | | |
| ጠቅላላ ወጪ /ከተከለሰ /Revised Plan/ | /In millions USD, Euro or other currency as per the agreement or Birr/ | | |
| በመ/ቤቱ ገቢ የሚሸፈን ወጪ | በብር | | |
| ፕሮጀክቱን የሚተገብረው አካል /አንዱን ይምረጡ/ | በራስ ኃይል | በኮንትራክተር | |
| የሚተገበርበት ቦታ | | | |
| ፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ አሁን ያለበት ደረጃ | | | |

### 2. የፕሮጀክቱ ዝርዝር መግለጫ

- መግቢያ፡
    - ስለ ፕሮጀክቱ ምንነት አጭር ገለጻ

[6] በልማት ድርጅቱ በኩል ለሚተገበር ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ የሚቀርብ

- በፕሮጀክቱ ምን ለማግኘት እንደታሰበ ጠቅለል ያለ ሐሳብ
- በሪፖርቱ ጊዜ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች

3. **የፊዝካል አፈጻጸም** (ይህ ክፍል የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራትን፣ በመለኪያ/መስፈርያ የተብራራ አፈጻጸም፣ ወዘተ ያቀርባል)

| የፕሮጀክቱ ኮምፖንቶችና ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | የበጀት ዓመቱ ክንውን | የበጀት ዓመቱ ክንውን በ% | ፕሮጀክቱ ከተጀመረ እስከ አሁን ያለው ክንውን በ% | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

4. **የፋይናንስ አፈጻጸም**

| ፕሮጀክቱ ኮምፖንቶችና ዋና ዋና ተግባራት | የገንዘቡ አይነት /Currency/ | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | የበጀት ዓመቱ ክንውን | የበጀት ዓመቱ ክንውን በ% | ፕሮጀክቱ ከተጀመረ እስከ አሁን ያለው ክንውን በ% | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

5. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ማቅረቢያ /ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ያጋጠሙና በመረጃ የተደገፉ ተጨባጭ ምክንያቶች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡/

| ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ | ትኩረት/ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች | ችግሩ እንዲፈታ የሚጠበቅበት ጊዜ | ችግሩን ለመፍታት በአስፈፃሚው መ/ቤት የተወሰደ እርምጃ | ችግሩን ለመፍታት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት አካል |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

6. በሪፖርቱ ጊዜ የተገኙ ትምህርቶች

7. የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ /Annual Working Plan/

| የፕሮግራሙ/ፕሮጀክቱ ኮምፖንቶችና ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የፊዚካል ዕቅድ | | | | የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን usd/euro…etc/ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

## 8. አባሪ

- ፕሮግራሙ ወይም ፕሮጀክቱ በልማት አጋር የሚደገፍ ከሆነ የስምምነት ሰነድ፤
- ፕሮጀክቱ የግንባታ ፕሮጀክት ከሆነ የኮንትራት ስምምነት ሰነዱ ስካን /scan/ ተደርጎ በሶፍት ኮፒ መቅረብ ይገባዋል፡፡

## Annex: - Progress Report Templates for Programs and Projects Financed by Development Partners /Doners/

**Table 9:- Summary of Programs and Projects implemented in 2012 EFY /In Millions/ with the support of Development Partners**

| Name of Program / Project | Name of Development Partner | Currency Type | Program/Project Duration | Total Aid/ Loan | Expnediture To date | Expenditure in 2012 EFY /2019-2020 GC/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | |
| 2. | | | | | | |
| 3. etc | | | | | | |

**Table 10:- Progress Report Template /Quarter, Semi-Annual, and Annual Reports**

1. **Program/Project Profile**

| | |
|---|---|
| **Name of Program/ Project** | |
| **Program/Project Duration** | |
| **Program/Project Commencement Date** | |
| **Program/Project End Date** | |
| **Program/Project Objectives** | |
| **Fund Source** | |
| **Total Amount of Fund** | |
| **Amount of Co-Finance** | |
| **Geographic Target Area /Region, Zone, District/** | |
| **Current Status of the Program/Project** | |
| **Key Stakeholders /Implementing Partners/** | |

2. **Introduction**
    2.1. **Background of the Program/Project**
    2.2. **Program/Project Objectives**
    2.3. **Program/Project Expected results**
3. **Achievement per Components or Outcomes and Activities /Naratives/**
    3.1. **Component or Outcome 1**
    3.2. **Component or Outcome 2**
    3.3. **Component or Outcome 3**
4. **Plan Vs Achievement /Physical Performance/**

| Description Per Componenets or Outcomes | Unit | Plan | Achievement | Achievement /%/ | Achievement to Date /%/ | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

5. **Financial Performance**

| Description/Activities Per Componenets or Outcomes | Currnecy | Annual Budget | Annual Expenditure | Performance in /%/ | Expenditure to Date /%/ | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |

**6. Key Challenges Eccountered /Issue Table/**

| Current Status of the Program/Project | Main Issue | Issue Resolution Expected date | Mitigation Measures taken by the implementing agency | Responsible Actors to solve the issue |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

**7. Lesson Learnt**

**8. Plan for the 2013 Budget Year /Annual Working Plan/**

| Program/Project Main Component & Main Activities | Unit | Physical Plan | | | | Financial Plan /In Millions USD/Euro…/ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1st Quarter | 2nd Quarter | 3rd Quarter | 4th Quarter | 1st Quarter | 2nd Quarter | 3rd Quarter | 4th Quarter |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |